# ያውልሽ ሀብሌ

አብርሃም በየነ ህዳር 2003

ያባቴን የእምነት ማተብ ቃሉን
የፍቅራችን ቋጠሮ ውሉን
ላንቺ ስል የፈታሁት ሀብሉን
የሞትን ሸክም መቀበሌን አይቼ
መለያየታችን አይቀሬነቱን ገምቼ
የላኩልሽን የሀብሉን ምስጢር ጥቅል
የትግሉ ነው ህይዎቴ‡‡.. ስል
እንዳይበጠስ ያባቴን ስጦታ ሀብል
በአደራ የተውኩልሽ ለፍቅሬ መከሰቻ
የመለያየታችን ቡታ ይሁንሽ ለሀዘንሽ ዳርቻ።

ስሚኝ ፍቅሬ‡‡ፍሬህይዎት
ያረገዘውን ደመና ሰማዩ ድንገት
የበጋ ደራሽ ውሃ የወንዝ ጎርፍ
ካደረገው በህይዎት እንደማልተርፍ
እወቂውና ሞቴን ባለመኖሬ ቆርጠሽ
በልብሽ ውስጥ ቅበሪኝ የሞት ሞቴን ተረድተሽ።

ፍሬህይዎት አብሮ አደጌ
ያውልሽ ሀብሌ የፍቅሬ ምስጢር ቋጠሮ
ያን ያደግንበትን የቤተሰብ ተፈጥሮ
የወለደውን መዋደድ ላለማስቀየም ብዬ
የደበቅሁትን ምስጢር ከሀብሌ ጋር ጠቅልዬ
የላኩለትን አደራ ከቡርነቱን አይቶ
ቀብሮኝ ይኑር ልብሽ በሙዳዩ ውስጥ ከቶ።

ፍሬህይዎት
እቱ ልበልሽ ጓዲት- ፍቅረኛዬ?
ወይንስ
የቃል ኪዳኔ ማተብ የትገሌ አጋር አለኝታዬ?
ለኔ ሁሉንም ነሽ የሞት የህይዎት ባልደረባ
አንቺን ትቼ እኔ ወደ መቃብር ስገባ
የሚሰማኝን ድብቅ ፍቅር ላብሮ አደጌ
ብሞትም አኖረዋለሁ በልቤ ትራስ ግርጌ።

ሰማሽ ፍሬህይዎት
ይሀን እምነት ሰንቄ ነው መጓዜ ወደ እስር ቤት
ያን ቃል የገባሁትን እዳ ልከፍል

የማይቀረውን ሞት ልሞት
ጽዋዬ ሞልቶ ሲደፋ ልጎነጨው ልሰዋለት
ሁሉንም ትቸው ለቀሪዎቹ ጽናት ብርታት
ስሰናበትሽ ምስጢሬን እንደቋጠርኩት
የትናንቱን ትውስታዬን በህብሌ ጫፍ ቋጥሬ
በልብሽ መቅደስ ልኑር እንደ ታቦት ተከብሬ።

ስሚኝ ፍሬህይዎት
ስማዩ በሞት ደመና ጥለግ ሲጠቁር
የምህላችን ቃል-ኪዳን ክርር
የእምነታችን ማተብ ሳይበጠስ
ደንጊያው ሲጫነኝ አፈር ስለብስ
በመጨረሻዋ ህቅታዬ ይህችን አለም ስሰናበት
በመቃው አንገትሽ ታስሮ በሀብሉ ጫፍ ቀለበት
የሚኖረውን ምስጢር የፍቅር ቃል አብነት
ያለምነውንም ህልም የራኢይውን ሕዝባዊነት
አንቺው አኑሪው አደራ ባንቺ ውስጥ እኔ ስሞት።

እስከዘላለሙ አፍቃሪሽ

በላይሁን

ለምርኮኛ-ፍሬህይዎት።